# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# የማኅበራት አስተዳደር ደንብ

**ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም**

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## የማኅበራት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ......./፳፻፲፫

### <u>መግቢያ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስም ማህበራት እየተበራከቱ የመጡበት ወቅት በመሆኑ ማኅበራት ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክቱት በጎ አስተዋጽዖ ሊኖር ስለሚገባ በቤተ ክርስቲያን አካላት ክትትል እየተደረገባቸው የሚቋቋሙበት ዓላማ መሠረት አድርጎ መደበኛ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሥራው በማኅበራቱ እየተደገፈ በአግባቡ መወጣት እንዲችል፣

በቤተ ክርስቲያን ስም እና መዋቅር ስር የሚቋቋሙ ማኅበራት የሚያቅፏቸው አባላት፣ የሚሰበስቡት ሀብትና ንብረት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አካላት ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግበት የሚያስችልን ሥርዓት የሚዘረጋ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ማኅበራት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ የበጎ አድራጎትና የልማት ሥራ ያላቸው አስተዋጽዖ እንዲጎለብት፣አመሠራረታቸው፣ አሠራራቸውና አገልግሎታቸው በታወቀ የቤተ ክርስቲያን ሕግ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የማኅበራት አስተዳደር ሥራን ለሚያስፈጽሙ የቤተ ክርስቲያን አካላት ግልጽ ተግባርና ኃላፊነት የሚሰጥ እና ማኅበራትን የሚመዘግቡበት፣ የሚቆጣጠሩበትና የማስተካከያ ውሳኔ የሚሰጡበት ሥነ ሥርዓት የሚደነግግ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በቤተ ክርስቲያን ስር የሚቋቋሙ ማኅበራት ለተመሠረቱበት ዓላማ ብቻ እንዲሰሩ የሚያደርግ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ቅዱስ ሲኖዶስ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፳፬ በተደነገገው መሠረት ይህንን የማኅበራት አስተዳደር ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፩

### አጭር ርዕስ

**ይህ ሕግ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማኅበራት አስተዳደር ደንብ ቁጥር---------/፳፻፲፫ ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፪

### ትርጓሜ

፩. "ቤተ ክርስቲያን" ማለት ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ ብላ የምታምን ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት፣ በሁሉ ያለች፣ አንዲትና ቅድስት የሆነች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡

፪. "ቅዱስ ሲኖዶስ" ማለት ቅዱስ ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጴስ ቆጶሳት የሚገኙበት ዓቢይ ጉባኤ ሆኖ ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ሕግ አውጪና ወሳኝ አካል ነው፡፡

፫. "የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባኤ›› ማለት መላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የሚገኙበት ጉባኤ ነው፡፡

፬. "ፓትርያርክ" ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አበው፣ አበ ብዙኃን እና መሪ ማለት ነው፡፡

፭. "ቋሚ ሲኖዶስ" ማለት ፓትርያርክ፣ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም አራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት/ጳጳሳት/ በአባልነት የሚገኙበት ጉባኤ ነው፡፡

፮. "የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት" የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እና ቋሚ ሲኖዶስ መነጋገሪያ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ የሚያቀርብ፣ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለሚመለከተው አካል የሚያስተላልፍና አፈጻጸሙን የሚከታተል ጽ/ቤት ነው፡፡

፯. "ሊቀ ጳጳስ" ማለት በሕገ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተሰጠው ትርጓሜ እንዳለ ሆኖ የማኅበራት ምዝገባ፣ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ የበላይ ኃላፊ ሆኖ የሚሠየም ሊቀ ጳጳስ ነው፡፡

፰. “ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፱. “ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ የተሠየመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ዋና የሥራ መሪ ነው፡፡

፲. “መምሪያ” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማኅበራት ምዝገባ፣ ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ ነው፡፡

፲፩. “ሀገረ ስብከት” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ተለይቶ የተከለለና በሊቀ ጳጳስ ወይም በኤጴስ ቆጶስ የሚመራ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ክልል ነው፡፡

፲፪. “ማኅበር” ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበ ማኅበር ነው፡፡

፲፫. “የአስተዳደር ጉባኤ” ማለት በየመዋቅሩ የበላይ ኃላፊዎች የሚመራ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚወስን አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

## አንቀጽ ፫

## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በዚኽ ደንብ በተፈቀደው አግባብ በሚቋቋሙ እና ይኽ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ተቋቁመው የነበሩ እና ምዝገባ እና ፈቃድ ባገኙ በሁሉም ማሕበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፬

## የደንቡ አተረጓጎም

፩. ይህ ደንብ ከሕገ ቤተ ክርስቲያን እና ከሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ /ቃለ አዋዲ/ እና ከሌሎች ደንቦች ጋር ተጣጥሞ ይተረጎማል፡፡

፪. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ያልተሟሉ በሆኑባቸው ጉዳይ ሁሉ እንደ አግባብነቱ በሕገ ቤተ ክርስቲያን እና በሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ ቃለ አዋዲ ድንጋጌዎች ይሸፈናል፡፡

፫. ማኅበራትን በሚመለከት ጉዳይ በዚኽ ደንብና በሌሎች ደንቦች መካከል ተቃርኖ ያለ እንደሆነ ገዥ የሚሆነው ይህ ደንብ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የማኅበራት አስተዳደር

### አንቀጽ ፭

### የማኅበራት አስተዳደር አካላት

ቤተ ክርስቲያን ማኅበራትን በሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ/ቃለ አዋዲ/ ድንጋጌ መሰረት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅሮች ሁሉ ትመራለች፤ታስተዳድራለች።

### አንቀጽ ፮

### የቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር

ቅዱስ ሲኖዶስ በሕገ ቤተክርስቲያንና በሌሎች ሕግጋት የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከማኅበራት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. በጠቅላይ ቤተክህነት ደረጃ የተመዘገበንና ለመመዝገብ የቀረበን የማኅበራት ምዝገባን፣ ስረዛን እንዲሁም ዕገዳን በሚመለከት በጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

፪. የይግባኝ ቅሬታ የቀረበበት የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ጉዳዩ ተጣርቶ እስኪወሰን ታግዶ እንዲቆይ የመወሰን ሥልጣን አለው።

፫. በጠቅላይ ቤተክህነት ደረጃ የተመዘገበንና ሊመዘገብ የሚገባውን የማኅበራት አስተዳደርን በሚመለከት የመጨረሻ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን እየመረመረ ውሳኔ ይሰጣል፣ መልካም የአገልግሎት ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።

### አንቀጽ 7

### የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላይ ቤተ ክህነት በሕገ ቤተክረስቲያንና በሌሎች የቤተክርስቲያን ሕግጋት የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከማኅበራት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. የማኅበራት ምዝገባን እና ስረዛን አስመልክቶ በመምሪያው ውሳኔ፤ በመምሪያው ሊቀ ጳጳስ በሚሰጥ እገዳ እንዲሁም በሀገረስብከት አስተዳደር ጉባዔ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን መርምሮ በአስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ይሰጣል።

፪. መምሪያው የማኅበራት አስተዳደርን በዚህ ደንብ መሠረት እየፈጸመ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

፫. የማኅበራት አስተዳደርን በሚመለከት ከመምሪያው ኃላፊ የሚቀርብለትን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ፤ በጀት እና ሪፖርት መርምሮ በአስተዳደር ጉባኤ ያጸድቃል።

፬. የማኅበራት አስተዳደርን በሚመለከት የመምሪያው ኃላፊና ምክትል ኃላፊን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ ይወስናል።

፭. ከማኅበራት አስተዳደር ጋር የተገናኙ ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ መፍትሔ ይሰጣል።

፮. የማኅበራት አስተዳደርን በሚመለከት መምሪያው በሚሰጣቸው ማናቸውም ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ቅሬታ በአስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ይሰጣል ።

## አንቀጽ 8

## የማኅበራት ምዝገባ፤ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

የማኅበራት ምዝገባ፤ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ማኅበራትን መመዝገብ ፣መደገፍ፣ማስተባበር፤

፪. ማኅበራት ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

፫. የማኅበራትን ዓመታዊ የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በዚህ ደንብ በተወሰነው መሠረት መመርመር፤

፬. የማኅበራቱ ማናቸውም ገንዘብ እና ንብረት በቤተ ክርስቲያኒቱ ሞዴላ ሞዴል እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ ደረሰኞችንም በአግባቡ ያሰራጫል፤አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፭. ማኅበራት ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የውስጥ አስተዳደር እና የራስ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠትና ተፈፃሚነቱን መከታተል፤

፮. ከሚመለከታቸው የሀገረ ስብከት የሥራ ክፍሎች ጋር በመተባበር በቤተ ክርስቲያን ስር የሚንቀሳቀሱ ማኅበራትን ቁጥር፣ የተሰማሩባቸውን አህጉረ ስብከትና የአገልግሎት ዘርፎች፣ የተጠቃሚዎቻቸውን እና የአባሎቻቸውን ብዛት እና መሰል መረጃዎች የሚይዝ የመረጃ ማዕከል ማቋቋም፤ መረጃዎችንም በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤

፯. ማኅበራትን በሚመለከት ከአህጉረ ስብከት የሥራ ክፍሎች ጋር እንዲሁም ከማኅበራቱ ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፤

፰. ማኅበራት ቤተ ክርስቲያን ለምታወጣቸው ሕጎችና መመሪያዎች ተገዢ እንዲሆኑ መሥራት፣

፱. ማኅበራት የሚያከናውኑት የልማት ሥራና የሚፈጽሙት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ከምታወጣቸው የልማትና መንፈሳዊ የአገልግሎት ዕቅዶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ መሥራት፤

፲. የማኅበራትን መተዳደሪያ ደንቦችና ማሻሻያዎቻቸውን ማረጋገጥና መመዝገብ፤

፲፩. በዚሕ ደንብ መሠረት የምዝገባና የሰነድ ማረጋገጥ አገልግሎት ክፍያ፤የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን ከማኅበራት በበጀት እና ሒሳብ መምሪያ በኩል እንዲሰበሰብ ማድረግ፤

፲፪. ማኅበራት በሕግ አግባብ ፈቃዳቸው ሲሰረዝ ወይም መፍረሳቸው ሲረጋገጥ በሒሳብ አጣሪነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን መመደብ እና ሥራቸውን በአግባባቡ ማከናወናቸውን መቆጣጠር፤

፲፫. ማኅበራት ከዚህ ሕግ ድንጋጌ ውጭ ሲሆኑ በዚህ ሕግ መሠረት ማገድ እና እንደአስፈላጊነቱ ጥፋት መፈጸማቸው ያለማስተባበያ በበቂ ሁኔታ እና ማስረጃ ሲረጋገጥ ፈቃዳቸውን መሠረዝ፤

፲፬. የማኅበራት የምዝገባ፤የፈቃድ አሰጣጥ፤ የሰነድ ማረጋገጥ፤ የአገልግሎት ክፍያ እና ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ የማውጣት፤

፲፭. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ ደንብ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለአህጉረ ስብከት በውክልና መስጠት፤

፲፮. መምሪያው ማኅበራት ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ሊያዘጋጅ ይችላል።

፲፯. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

## ክፍል ሦስት

## የማኅበራት አመሠራረትና ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## አንቀጽ 9

## መርሆች

የማኅበራት አመሠራረት በሚከተሉት መርሆች ይመራል:-

፩. ማንኛውም ማኅበር ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፣

፪. በማኅበራት ውስጥ አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ አባል በፈለገ ጊዜ ከማኅበር መውጣት ይችላል፤

፫. ማንኛውም ማኅበር ከመምሪያው በሚወርድ ዝቅተኛ የአባልነት መስፈርቶች በተጨማሪ የአባላት መቀበያ መሥፈርቶችን የመወሰን መብት አለው፤

፬. ማንኛውም ሰው የማኅበሩን መስፈርት ሲያሟላ አባል የመሆን መብት አለው፤

፭. እያንዳንዱ አባል እኩል ድምፅ አለው፤

፮. ማኅበራት ለአባላት ትርፍ ለማከፋፈል በማሰብ ሊቋቋሙ አይችሉም፤

፯. የማኅበራት አመሠራረትና የውስጥ አሰራር የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ታሪክ እና ትውፊት ያከበረ፣ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ አስራር ተገዢ የሆነ፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል፤

፰. ማንኛውም ማኅበር የሚመራው በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው፤

፱. ማንኛውም ማኅበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም።

፲. ማንኛውም ማኅበር አባላቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባል እና የንሰሀ አባትም ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

፲፩. ማንኛውም ማኅበር አባላቱ ትምህርተ ሃማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ዝግጁ የሆኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## <u>አንቀጽ ፲</u>

## <u>የማኅበራት ዓላማ</u>

ማኅበራት ዝርዝር ዓላማቸው በደንባቸው ላይ የተገለጸ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዓላማዎች መሰረት አድርገው ይቋቋማሉ፤፦

፩. ትምህርተ ሃይማኖት ለሁሉም እንዲዳረስ ለሚሰሩ ተጠሪ መዋቅራዊ ተቋማት ድጋፍ መስጠት፤

፪. የቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑ ምዕመናን በቤተክርስቲያን አገልግሎት ተካፋይ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣

፫. ምዕመናን ቤተ ክርስቲያንን በእውቀታቸው፣ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው እንዲያገለግሉ የማሳወቅና የማስተባበር ሥራ ላይ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣

፬. በቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ቀኖና፣ታሪክ፤ ትውፊት እና በአብነት ትምህርት ቤቶቿ እንዲሁም ልማታዊ ተግባራት ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማድረግ በሚመለከተው የሊቃውንት ጉባዔ ታይቶ እንዲጸድቅ ማድረግ እና ለተግባራዊነቱ ከሚመለከተው መዋቅራዊ አካል ጋር በጋራ ሆኖ ለውጤት መትጋት ፣

፭. በጎ አድራጊ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በማስተባበር ገዳማትን፤ የአብነት ትምሕርት ቤቶችን፤ ቅርሶችን፤በተለያየ ጊዜ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ለሚደርሱ ጉዳቶች የመልሶ ማቋቋም እና ድጋፍ ከሚሰሩ መዋቅራዊ ተቋማት ጋር በጋራ መስራት እና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤

፮. የቤተ ክርስቲያንን ቅርሶችና ሀብቶች በአግባቡ ለምዕመናን እንዲሁም ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ዜጎች የማሳወቅ ስራን ከሚመለከተው መዋቅራዊ አካል ጋር በጋራ መስራት እና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

፯. በተለያዩ ምክንያቶች የተዘጉ ወይም አገልግሎታቸው ያልተሟላ አቢያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ እና አገልግሎት እንዲሰጡ ከሚመለከተው መዋቅራዊ አካል ጋር በጋራ መስራት እና ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፤

፰. ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊ ሥነ ምግባር በምዕመናን ዘንድ እንዲጎለብት እና እንዲጠናከር ለሚመለከተው መዋቅራዊ ክፍል ድጋፍ መስጠት እና በጋራ መስራት፤

፱. ካህናት እና ምዕመናን መንፈሳዊ ይዘቱን በጠበቀ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የመረዳዳት ሕይወታቸው እንዲበረቱ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከተው መዋቅራዊ አካል ጋር በጋራ ማከናወን እና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

፲. ሌሎች ከቤተ ክርስቲያን ዓላማ ጋር የማይቃረኑ በጎ መንፈሳዊ ተግባራትን ስልጣን ካለው ከቤተ ክርስቲያኗ መዋቅራዊ ክፍል ጋር በመናበብ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት እና ትብብር ማድረግ፡፡

## <u>አንቀጽ ፲፩</u>

## <u>የማኅበራት ዓይነቶች</u>

፩. ማኅበር፡-

ሀ/ ጠቅላላ ማኅበር

ለ/ የሙያ ማኅበር

ሐ/ የማኅበራት አንድነት ኅብረት

መ/ የሐዋሪያት የአንድነት ኑሮ ማኅበር

ሠ/ መንፈሳዊ የአስጎብኚ ማኅበር

ረ/ መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር

ሰ/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴ

ሸ/ ሁለገብ መንፈሳዊ አገልግሎት ማኅበር

፪. "ጠቅላላ ማኅበር" ማለት፡- ቁጥራቸው 750/ሰባት መቶ ሃምሳ/ እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፤ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ሙሉ ፈቃደኛ በሆኑ አባላት የሚቋቋም፣ የተቋቋመበትን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አህጉረ ስብከት የሚፈጽምና እና ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ማኅበር ነው፤

፫. "የማሕበራት አንድነት ህብረት"፡- በጠቅላላ ማሕበር ቅርጽ የተቋቋሙ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ማኅበራት የጋራ ዓላማቸውን ለመፈጸም ሕብረት በመፍጠር የሚመሰርቱት ሲሆን ቁጥሩም ከ1/አንድ/ በላይ ሊሆን የማይችል ነው።

፬. "የሙያ ማኅበር" ማለት፡- በተመሳሳይ ሙያ ያሉ/የተመረቁ/ ቁጥራቸው 24/ሃያ አራት/ እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፤ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ሙሉ ፈቃደኛ በሆኑ አባላት የሚመሰረት ሲሆን፤ አባላቱ ባላቸው ዕውቀት እና ልምድ መሰረት ቤተ ክርስቲያንን በሚጠቅሙ ልዩ ልዩ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን እና የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም፣ አገልግሎቱን ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አህጉረ ስብከት የሚፈጽም እና ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ማኅበር ነው።

፭. "የሐዋርያት አንድነት ኑሮ ማኅበር"፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፤ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ሙሉ ፈቃደኛ በሆኑ አባላት የሚቋቋም፣ አባላቱም በመንፈሳዊ ሕይወት ታንጸው በዓለም እየኖሩ በዕውቀታቸው፤በጉልበታቸው እና በገንዘባቸው ከማናቸውም ገቢ የሚያገኙትን ሀብትና ንብረታቸውን ለጋራ መንፈሳዊ ዓላማ በማዋል በአንድነት የሐዋርያትን ኑሮ ለመኖር በቁጥር 12/አስራ ሁለት/ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ነው።

፮. "መንፈሳዊ የአስጎብኚ ማኅበር" ቁጥራቸው 12/አስራ ሁለት/ እና ከዚያ በላይ የሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፤ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ እና ጠንቅቀው የሚያውቁ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ቅርሶች ላይ በቂ እውቀት ባላቸው አባላት የሚቋቋም፣ ሆኖ ዓላማውም የቤተ ክርስቲያንን

ቅርስ፣ሀብት፣ሥርዓት፣ታሪክ እና ትውፊት ለሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ ለሚመጡ ጎብኝዎች ታሪክን እና ትውፊትን ሳያፋልሱ በአግባቡ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ እና የሚያስጎበኙ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

፯. "መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር" ቁጥራቸው 12/አስራ ሁለት/ እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፣ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ሙሉ ፈቃደኛ በሆኑ አባላት የሚቋቋም ሆኖ ዓላማውም የተለያዩ ጥንታዊ ገዳማትን እና አድባራትን እንዲሁም ታሪካዊ እና ትውፊታዊ መንፈሳዊ ቦታዎችን ለመጎብኘት እና መንፈሳዊ በረከትን ለማግኘት እና ለማስገኘት በማሰብ ለብዙኃን መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም ማኅበር ነው፡፡

፰. "የበጎ አድራጎት ኮሚቴ" ማለት ቁጥራቸው 5 /አምስት/ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ እና የሰበካ ጉባዔ አባላት በሆኑ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለአንድ የቤተ ክርስቲያን አስቸኳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ከሕዝብ ለመሰብሰብ ለመርዳት ለመደገፍ ዓላማና ግብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

፱. "ሁለገብ መንፈሳዊ አገልግሎት ማኅበር" በአንድ ሀገረስብከት ቁጥራቸው ከ250/ሁለት መቶ ሃምሳ/ በላይ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ፣ የሰበካ ጉባዔ አባላት እና ትምህርተ ሃይማኖትን የተማሩ ወይም ለመማር ሙሉ ፈቃደኛ በሆኑ አባላት በማሕበሩ መተዳደርያ ደንብ እና መመስረቻ ጽሁፍ የዓላማ ይዘት እየተመዘነ ውስን ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ፈቃደኛ በሆኑ ምዕመናን የሚቋቋም ማኅበር ነው፡፡

፲. መምሪያው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ማሕበራት ፈቃድን በተመለከተ ተገቢውን ጥናት በማድረግ እያቀረበ ሲወሰን የማህበራቱን ዓይነት እና ፈቃድ ሰጭውን እየለየ በማቅረብ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፲፩. አንድ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ያለው ሆኖ ሊደራጅ ይችላል፡፡ የማኅበሩ አወቃቀርና አስተዳደር በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡

፲፪. የጽዋዕ ማሕበራትንና ሰንበቴዎችን በተመለከተ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ይወጣላቸዋል፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የማኅበራት ምዝገባ ሥርዓት

## አንቀጽ ፲፪

## ምዝገባ

፩. ማንኛውም ማኅበር በዚህ ደንብ መሠረት መመዝገብ አለበት፡፡

፪. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩/፩/ሀ-ሠ// ድረስ ያሉ ማኅበራትን የመመዝገብ፤ፈቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ስልጣን የጠቅላይ ቤተ ክሕነት የማኅበራት ምዝገባ፤ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ ተግባር ነው፡፡ ከአንድ ሀገረ ስብከት በላይ ለሚደረግ የመንፈሳዊ ጉብኝት ለማካሄድ የሚቋቋሙ ማሕበራትን የመመዝገብ ስልጣን የመምሪያው ይሆናል፡፡

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩/፩/ሠ-ሽ// ድረስ ያሉ ማኅበራትን የመመዝገብ፤ፈቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ስልጣን የሀገረስብከቶች ተግባር ነው፡፡ በሀገረስብከቱ ስር ለሚደረጉ የመንፈሳዊ ጉብኝት ለማካሄድ የሚቋቋሙ ማሕበራትን የመመዝገብ ስልጣን የሀገረ ስብከቱ ይሆናል፡፡

፬. የማኅበር ምዝገባ ማመልከቻ እና ተያያዥ ሕጋዊ ሰነዶች በቀረቡ በ፵፭ ቀናት ውስጥ በዚህ ደንብ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ስልጣን ያለው አካል ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ማኅበሩን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፭. አመልካቹ ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያልተሰጠው እንደሆነ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን

፭.፩. መዝጋቢው የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ መምሪያ እንደሆነ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ቅሬታውን ያቀርባል፤ ዋና ሥራ አስኪያጁ ቅሬታውን ተቀብሎ በአስተዳደር ጉባዔ በ፴/ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በተጠቀሰው ቀን ምላሽ ያልሰጠ እና በውሳኔው ቅሬታ ያደረበት አካል ለቅዱስ ሲኖዶስ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

፭.፪. መዝጋቢው ባለስልጣን ተቋም ሀገረስብከት እንደሆነ ለሀገረስብከቱ ሊቀ ጳጳስ/ጳጳስ ቅሬታውን ያቀርባል፤ ሊቀ ጳጳሱ ቅሬታውን ተቀብሎ በአስተዳደር ጉባዔ በ፴/ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በተጠቀሰው ቀን ምላሽ ያልሰጠ እና በውሳኔው ቅሬታ ያደረበት አካል ለጠቅላይ ቤተ ክሕነት ማሕበራት ምዝገባ፤ክትትል እና ቁጥጥር መምሪያ አቤቱታ በማቅረብ አቤቱታውም በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ እንዲመራ ሁኖ በአስተዳደር ጉባዔ ውሳኔ ያገኛል፡፡ የአስተዳር ጉባዔው ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

፮.ይግባኝ ሰሚው የቀረበለትን ቅሬታ በመመርመር በ60/ስልሳ/ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲.መዝጋቢው ማኅበሩን ያልመዘገበው ያለበቂ ምክንያት መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ሲረዳ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ወዲያውኑ እንዲሰጥ ያዛል፡፡ ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም፣ መዝጋቢው ለቀረበለት የምዝገባ ማመልከቻ በንዑስ አንቀጽ ፭ በተመለከተው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ፣ ማኅበሩን ላለመመዝገብ በቂ ምክንያት እንደሌለው ይቆጠራል፡፡

፲፩. ማንኛውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ለመሥራት የሚፈልግ ማኅበር በዚህ ሕግ ሳይመዘገብ ሊሠራ ፈጽሞ አይችልም፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ስም ይዞ ሳይመዘገብ እና ህጋዊ ፈቃድ ሳይሰጠው የሚንቀሳቀስ ማኅበር በሙሉ ሕገ ወጥ ነው፡፡

## አንቀጽ ፲፫

## ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

፩. የማኅበራት የምዝገባ ማመልከቻ በማኅበሩ መሥራቾች ሰብሳቢ ተፈርሞ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል:-

(ሀ) የመሥራቾችን ሥም፣ አድራሻና ዜግነት የያዘ የምሥረታ ቃለ-ጉባኤ፣

(ለ) የመሥራቾች የመታወቂያ ወይም የፓስፖርት እና የሰበካ ጉባኤ አባልነት መታወቂያ ኮፒ፣

(ሐ) የማኅበሩን ሥም እንዲሁም ዓርማ (ካለው)፣

(መ) የማኅበሩን ዓላማ እና ሊሰማራ ያሰበበትን የአገልግሎት ዘርፍ፣

(ሠ) ሊሰማራ ያሰበበትን የአገልግሎት ቦታ፣

(ረ) በመሥራቾች የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ፣

(ሰ) የማኅበሩን አድራሻ፣

፪. አመልካቹ መምሪያው በሚያወጣው የክፍያ መመሪያ የሚወስነውን የምዝገባ ክፍያ በየደረጃው ይከፍላል፡፡

## አንቀጽ ፲፬

## የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል

፩. መዝጋቢው ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ መኖሩን ካረጋገጠ ማኅበሩን አይመዘግብም:-

(ሀ) ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲የዋና ዓላማን መሰረት ያላደረገ እና በአንቀጽ ፲፫ የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝና ይህንንም እንዲያስተካክል የአመልካቹ ተወካይ ተጠይቆ ለማስተካከል ካልቻለ፣

(ለ) የማኅበሩ ዓላማ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተመለከተው የአገልግሎት ዝርዝር ዓላማ ለሕግ ወይም ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት ተቃራኒ ከሆነ፤

(ሐ) ማኅበሩ የሚመዘገብበት ሥም ወይም ዓርማ፣ ከሌላ ማኅበር ወይም ከማንኛውም ሌላ የቤተ ክርስቲያን ተቋም ሥም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም ሕግን ወይም የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ዶግማና ቀኖና የሚቃረን ከሆነ፤

(መ) ማኅበሩ ለምዝገባ ያቀረበው ሰነድ በሐሰት የተዘጋጀ ወይም የተጭበረበረ ከሆነ።

፪. በዚህ ደንብ በግልጽ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ በአሠራርም ይሁን መመሪያ በማውጣት የምዝገባ ጥያቄን ሊከለክል አይችልም።

፫. ማመልከቻውን በዚህ ደንብ መሠረት መርምሮ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ አመልካቹ የጎደለውን ነገር በ፴ ቀናት ውስጥ አስተካክሎ እንዲቀርብ መዝጋቢው /ፈቃድ ሰጪው/ በጽሑፍ መልስ ይሰጠዋል።

፬. አመልካቹ የተባለውን ለማስተካከል ፈቃደኛ ካልሆነ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ሕጋዊ ምክንያት በመጥቀስ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል።

፭. የምዝገባ ጥያቄው ውድቅ የሆነበት አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በ፴ ቀናት ውስጥ ደረጃውን ጠብቆ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

## <u>አንቀጽ ፲፭</u>

## <u>ለምዝገባ ጥያቄ የሚቀርብ የማኅበራት መተዳደሪያ ደንብ ይዘት</u>

ማንኛውም ማኅበር የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመተዳደሪያ ደንብ ሊኖረው ይገባል፡-

፩. የማኅበሩን ስም እና ዓላማዎች፤

፪. የማኅበሩ የበላይ አካል፤ ሥልጣንና ተግባር፣ የውስጥ አደረጃጀትና አስተዳደር፣ የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፤

፫. የሥራ አመራር ኃላፊዎች የሚሾሙበትና የሚሻሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፤

፬.የሥራ አስፈጻሚ አካላት የሚሾምበትና የተጠሪነት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፣

፭. የማኅበሩ ገቢና ሐብት ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች በሕግ ከተፈቀደ የአገልግሎት ክፍያ በቀር ሊከፋፈል የማይችል መሆኑን፤

፮.የማኅበሩ አባል ወይም ሠራተኛ በመሆኑ ብቻ በማኅበሩ ንብረት ላይ አንዳችም መብት የማይኖረው መሆኑን፤

፯.ማኅበሩ ከአባላት የተለየ የራሱ መለያና የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን፤

፰.የአባላት መለዋወጥ በማኅበሩ ሕልውና ላይ ተጽዕኖ የሌለው መሆኑን፤

፱.ማኅበሩ ከማናቸውም ፖለቲካ፤ዘር እና ቋንቋን መሰረት በማድረግ መደራጀት እንደማይቻል እና ከወገንተኝነት የጸዳ መሆኑን፤

፲. በማናቸውም የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደራዊ ጉዳይ እና ውሳኔዎች ጣልቃ የማይገባ መሆኑን፤

፲፩.ቤተ ክርስቲያን በቃለ ዓዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ የተደነገጉትን ልዩ ልዩ ገቢዎች የማይሰበስብ እና የማይመለከተው መሆኑን፤

፲፪.የማኅበሩ የሒሳብና የገንዘብ እንቅስቃሴ ተቀባይነት ባለው የቤተ ክርስቲያን ሒሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚመራ መሆኑን፤

፲፫.የማኅበሩን የሥራና የሒሳብ ዕቅድና አፈጻጸም የሚመረምረውና የሚያጸድቀው የበላይ አካል መሆኑን፤

፲፬.ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች እና አባልነት የሚቋረጥባቸውን ወይም የሚታገድባቸውን ምክንያቶች፤ እንዲሁም አባልነት ሲቋረጥ ወይም ሲታገድ በማኅበሩ ውስጥ ይግባኝ የሚጠየቅበት ሥርዓት፣

፲፭.የአባልነትና ሌሎች ክፍያዎች የሚወሰኑበትና የሚጠየቁበት ሥርዓት፤

፲፮.አገልግሎቱን ከየትኛው የቤተ ክርስቲያን የሥራ ክፍል ጋር በመተባበር እንደሚፈጽም፤

፲፯.ማኅበሩ እንዲፈርስ ወይም እንዲዘጋ የሚወስነውን የበላይ አካልና የሚመራበትን ሥርዓት፤ ማኅበሩ ሲፈርስ ያለበትን ሕጋዊ ዕዳ ከፍሎ ተራፊው ንብረት ወይም ገንዘብ ፈቃዱን ለሰጠው

፲፰.የቤተ ክርስቲያን ተቋም የሚተላለፍ መሆኑን።

፲፱.የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚሻሻልበትን ሥርዓት እና የበጀት ዓመት፤

## አንቀጽ ፲፯

## የምዝገባ ውጤት

በዚህ ደንብ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ የተመዘገበ ማኅበር፡-

፩. ከቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ሰውነት የሚመነጭ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፤

፪. በሥሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ውል ይዋዋላል፤

፫. በስሙ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የመሆን፣ ንብረት የማስተዳደር መብት አለው፣

## አንቀጽ ፲፯

## የአገልግሎት ነጻነት

ማንኛውም ማኅበር የተቋቋመበትን የአገልግሎት ዓላማ ለማሳካት በቤተ ክርስቲያኗ ሕግ፤ደንብ እና መመሪያ መሰረት በተፈቀደለት ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት መብት አለው።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ምዝገባ ሥርዓት

### አንቀጽ ፲፰

### የበጎ አድራጎት ኮሚቴን ስለማጽደቅ

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ በሚመለከተው የቤተ ክርስቲያን ተቋም ሳይጸድቅ ገንዘብም ሆነ ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውም ድርጊት መፈፀም አይችልም።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፫. መዝጋቢው የቤተ ክርስቲያን ተቋም የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያጸድቅ የዚህን ደንብ አንቀጽ ፲፫ እና ፲፬ ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት።

### አንቀጽ ፲፱

### የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አደረጃጀትና ቆይታ

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴን የሚያቋቁም ውሳኔ መሥራች አባላቱን፣ የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ሰብሳቢ፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል።

፪. ውሳኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ዓላማዎች እና ዓላማዎቹን የሚያሳካበትን ጊዜ መግለፅ ይኖርበታል።

፫. ውሳኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል።

፬. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ሊጸድቅ የሚችለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው። መምሪያው ከኮሚቴው የሚቀርብለትን ሪፖርትና የሥራውን አስፈላጊነት በመመርመር ለተጨማሪ አንድ ዓመት ብቻ ፈቃዱን ሊያራዝም ይችላል።

፭. ሆኖም ግን የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ራሱን በዚህ ደንብ ላይ ከተጠቀሱት በማናቸውም ማኅበራት ቅርጽ ማደራጀት እና አገልግሎቱን ማስቀጠል የፈለገ እንደሆነ ቅድመ ሁኔታዎቹን አሟልቶ ሲገኝ ሊፈቀድለት ይችላል።

### አንቀጽ ፳

### የበጎ አድራጎት የሂሳብ መግለጫ

፩. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለፈቃድ ሰጭው አካል ማቅረብ አለበት።

፪. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተቋቋመው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ እንዳለቀ የሒሳብ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ ፳፩

## የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አባላት ኃላፊነት

፩. ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገውን በተመለከተ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል ወይም ተጠቃሚ እና ፈቃድ ሰጪው በኮሚቴው አባላት ላይ በቤተ ክርስቲያኗ ሕግ እና ሥርዓት መሠረት ስልጣን ላለው መዋቅራዊ አካል ክስ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ፳፪

## በቂ ያልሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት

፩. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት የኮሚቴውን ዓላማ ለማሳካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሳኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፀደቀው ውሳኔ ውስጥ የተመለከተ ነገር ከሌለ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ላቋቋመው ወይም ፈቃድ ለሰጠው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ገቢ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፳፫

## ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት

፩. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሳኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፀደቀው ውሳኔ ውስጥ የተመለከተ ነገር ከሌለ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ላቋቋመው ወይም ፈቃድ ለሰጠው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ገቢ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማኅበራት ሒሳብ አያያዝና ሪፖርት ሥርዓት

## አንቀጽ ፳፬

## የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ እና ስለወጪ አስተዳደር

፩. ማናቸውም ማኅበር የማኅበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ተቀባይነት ባለው የቤተ ክርስቲያን የሒሳብ አሰራር የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

፪. የሒሳብ ሰነዶቹ የማኅበሩን ገቢና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሐብትና ዕዳ፣ የለጋሾችን ማንነትና የገቢውን ምንጭ ያካተቱ መሆን አለባቸው።

፫. ማኅበራት በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሒሳብ ሰነዶችን፣ የሒሳብ ዓመቱ ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለአምስት ዓመት ጠብቀው የማቆየት ግዴታ አለባቸው።

፬. ማናቸውም ማኅበር ከሚያገኘው ማናቸውም ገቢ 70%/ሰላሳ ፐርሰንት/ ያኽሉን ለተቋቋመበት ዓላማ ብቻ የማዋል ኃላፊነት አለበት። ቀሪውን 30%/ሰላሳ ፐርሰንት/ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ያውላል።

## አንቀጽ ፳፩

## ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫና ምርመራ

፩. ማንኛውም ማኅበር ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሠረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ላቋቋመው ወይም ፈቃድ ለሰጠው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በአድራሻው መላክ አለበት።

፪. የማንኛውም ማኅበር ሒሳብ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ ፫ ወራት ውስጥ በቤተክርስቲያኒቱ መዋቅር ባለ የውስጥ ኢዲተር ይመረመራል እንደአስፈላጊነቱም በተመሰከረለት የውጭ የሂሳብ አዋቂ ሊመረመር ይችላል።

፫. አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የድርጅቱ አባላት ወይም ለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከማኅበሩ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያላቸው አካላት የሒሳብ ምርመራ እንዲደረግ ከጠየቁ ፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የማኅበር ሒሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል።

፬. የማኅበሩ ሒሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ እና ይህንን ለመፈጸም ማኅበሩ ፈቃደኛ ካልሆነ መዝጋቢው የውጭ ኦዲተር ሹሞ ማስመርመር ይችላል፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ መሠረት በፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጪ የሚከፍለው የሚመለከተው ማኅበር ይሆናል።

## አንቀጽ ፳፪

## ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

፩. ማንኛውም ማኅበር የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች የሚያሳይ ሪፖርት የሒሳብ ዓመቱ ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ማቅረብ አለበት።

፪. ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ሲቀርብ የሒሳብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት፡፡

፫. ፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የቀረበለትን ሪፖርት በመመርመር ማኅበሩ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፳፯

## የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት

፩. ማንኛውም ማኅበር የባንክ ሒሳብ ለመክፈት በቅድሚያ በተቅላይ ቤተክህነት ደረጃ የተቋቋመው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት፣በሀገረ ስብከት ደረጃ የተቋቋመው ከሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ስልጣን ባለው አካል በጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ የባንክ ሒሳብ ለመክፈት ጥያቄ የቀረበለት ፈቃድ ሰጭ ጥያቄው በቀረበለት በ፸ ቀናት ውስጥ ምላሽ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

፪. የማኅበራቱ ማናቸውም ገንዘብ እና ንብረት በቤተ ክርስቲያኒቱ ሞዴላ ሞዴል መሰብሰብ አለበት፡፡

፫. የማንኛውም ማኅበር የገንዘብ እንቅስቃሴ ፈቃድ በተሰጠው በስሙ በተከፈተ የባንክ ሒሳብ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አግባብ ውጭ የተከፈተ ማናቸውም የባንክ ሂሳብ ሕገ ወጥ ነው፡፡

፬. የማኅበር የባንክ ሒሳብ እንቅስቃሴ በመተዳደሪያ ደንቡ በተመለከተው አኳኋን ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

## ሕግ ስለማስከበር

## አንቀጽ ፳፰

## ምርመራ የማድረግ ሥልጣን

፩. ከቤተ ክርስቲያን አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከማኅበር አባላት ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ማናቸውም ማኅበር ሥራውን በሕግ መሠረት እየሠራ ስለመሆኑ ፈቃድ ሰጪው ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ቢኖርም ፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው ምርመራ ለማድረግ ሲወስን ምርመራውን ለማከናወን በቂ ምክንያት መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫. የምርመራ ሥራዎች በተቻለ ፍጥነት በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁና የማኅበሩን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ፈቃድ ሰጪው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

፬. ፈቃድ ሰጪው የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት፣ ከባድ የሕግ ጥሰት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና በዚህ ምክንያትም የማኅበሩን እንቅስቃሴ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጠቅላይ ቤተ ክህነት ደረጃ የመምሪያው የበላይ ኃላፊ ሊቀ ጳጳስ፤ ከሀገረ ስብከት እስከ አጥቢያ ላለው በፈቃድ ሰጪው ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የዕገዳ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት እግድ የተሰጠበት ማኅበር በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪/፮-፰/ ላይ በተገለጸው የቅሬታ አቀራረብ ሂደት እና ጊዜ ደረጃውን ጠብቆ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ ፳፱</u>

## <u>አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ</u>

፩. ይህን ደንብ እና ሌሎች ሕጎችን ለሚጥሱ ማኅበራት ፈቃድ ሰጪው ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪. የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ ሆኖ፣ የተፈጸመውን የሕግ ጥሰት፣ ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተካከል እንዳለበት በግልጽ ማሳየት አለበት፡፡ ለማስተካከያ የሚሰጠው ጊዜ የተፈጸመውን ጉድለት ወይም ጥፋት ክብደትና የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፫. አንድ ማኅበር በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ወይም የፈጸመው ጥፋት ከባድ መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ሲያምንበት ለማኅበሩ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፬. በንዑስ አንቀጽ ፫ በተሰጠው ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መሠረት አሠራሩን የማያስተካክል ማኅበር ባጋጠመ ጊዜ ማኅበሩ እንዲታገድ ሊወስን ይችላል፡፡ ውሳኔው በይግባኝ ካልተነሳ ወይም ካልታገደ በቀር የዕገዳ ውሳኔው በተሰጠ በሦስት ወራት ውስጥ ማስተካከያ ያላደረገ ማኅበር ፈቃዱ እንዲሰረዝ በአስተዳደር ጉባኤው ይወስናል፡፡

፫. በአስተዳደር ጉባኤ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ውሳኔ የተሰጠበት ማኅበር አባላት፣ መሥራቾች ወይም ኃላፊዎች ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪/፮-፰/ ላይ በተገለጸው የቅሬታ አቀራረብ ሂደት ደረጃውን ጠብቆ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ፴

## የመስማት መብት

ፈቃድ ሰጪው ወይም መዝጋቢው በማንኛውም ማኅበር ላይ የትኛውንም ዓይነት አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ማኅበሩ መከራከሪያዎቹንና ማስረጃዎቹን የማቅረብና የመስማት መብቱን ማክበር አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ፴፩

## ደንቡን ስለማሻሻል

፩. ይህ ሕገ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

፪. ከሦስት አንድ እጅ (1/3ኛ) የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የማሻሻያ ጥያቄ ሲያቀርቡና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፴፪

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩. ከየትኛውም የቤተ ክርስቲያን አካል ፈቃድ አግኝተውም ሆነ ፈቃድ ሳይኖራቸው በተለያየ አገልግሎት ተሰማርተው እያገለገሉ የሚገኙ ማኅበራት ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት መመዝገብ አለባቸው፡፡

፪. ይሕ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ አግኝተው በተለያየ አገልግሎት ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ማኅበራት ፈቃዳቸው ጸንቶ የሚቆይ ሆኖ በፈቃድ ሰጭው አካል ታቅፈው ተገቢው የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

፫. በንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ያልተመዘገበ እና ፈቃድ ያልተሰጠው ማኅበር ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በቤተ ክርስቲያን እውቅና አይኖረውም፡፡

## **አንቀጽ ፴፫**

## **ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ**

**ይህ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ከጸደቀበት ከጥቅምት ፳፻፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡**

**አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**

**ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሐይማኖት**

**ጥቅምት ፳፻፲፩ ዓ.ም**